# ወያኔዎች በደመ-ነፍስ ከሚኖሩ እንስሳትና ነፍሳት አይሻሉም ፤

# ምክንያቱም የዛሬን ብቻ እንጂ የትላቱና የነገን ማሰብ አይችሉም !

በርሃንደጅ ሃሰን (**9 March 2017**)

የሕይወትን ወይም የመኖርን ትርጉም የምናውቀው ሞት ስላለ ነው ፣የወጣትነትን ትርጉም የምናውቀወ እርጅና ስላለ ነው ፣ የጨለማን ትርጉም የምናውቀው መብራት ስላለ ነው ፣የለሊትን ትርጉም የምናውቀው የቀን ፀሐይ ስላለ ነው ፣ ድሃን- ድሃ መሆኑን የምናውቀው ሃብታም ሰላለ ነው ፣ የሰነፍ ተማሪ ሰነፍና የሚታወቀው በቱጉህ ተማሪ ውጤት ነው ፣ ፉንጋን-ፉንጋ የሚያሰኛት ቆንጆዎች ስላሉ ነው ፣የሰነፍ ሠራተኛ ሠነፍና የሚታወቀው ታታሪ ሠራተኛ በመኖሩ ነው ወዘተርፈ ።ፍሬደሪክ ኤንጅል ስ የተፈጥሮ ሕግጋት (**Dialects of Nature**) በተሰኘው መጻሓፉ“ያለተቃ ራኒዩ የተፈጠረ ፣ የኖረና የሚኖር ነገረ የለም” እንዳለው ሁሉ ፤የማሰብ ጭ ንቅላት ወይም ችሎታ ያለው ፍጡር (ሰው) ባይኖር በደመነፍስ ሰለሚኖ ፍጡሮች (ግኝትዎች) ምንነት ባልታወቀ ነበር።

የደመ-ነፍስነት ሳይንሳዊ ትርጉምና ትንተና- ለሥነፍጥረት ተመራማሪ ሊሂቃን - ለ (ዚዮሎ ጂስቶች ፣ ኢንቲሞሎጂስቶች ፣ ሚሚኮሎጂስቶች ፣ ኦርኒስቶሎጂስቶች ) ወዘተ.. ትቼ 'የደመነፍስ' (**instinct**) ይፋ ትርጉም (በኢማሰብ ፣ በኢንቃት ፣ በኢማስተዋል ) ወይም 'በዳበሳ' - መንቀሳቀስ ፣ መኳዝ ፣ መኖር ወዘተርፈ ማለት ነው ።

መፍጠርም ሆነ ማምረት ስለማይችሉ ፣ የቅርቡና የሩቁን ፣የትላንቱና የነገን ማስብ ስለማይችሉ ፤ በደመ-ነፍስ የሚኖሩ ፉጥሮች ( ግኝትዎች) ሕይወት አጠረም ረዘመ ሕልው የሆኑበትን አካባቢ የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም ፣ በመበዝበዝ እና በመደምሰስ ተፈጥሮ የለገሳቸውን የአልሞትባይ ተጋዳይ (**existentialism**) ጥበብ በመጠቀም ከደቂቃ ወደ ደቂቃ ፣ከሰዓት ወደ ሰዓት ፣ ከዕለት ወደ ዕለት ወዘተ.. ሕይወታቸውን ለማቆየት ይፍጨረጨራሉ ። መዋለድ በማሰብ ወይም ባለማሰብ የተገደ በ የሥነ-ፍጥረት ሕግ ስላልሆነ - ዘር ተክተው ያልፋሉ ።

ከበርካታ የሰው ዘር ተሰጦዎች ወይም ችሎታዎች አንዱ እለት ከእለት ከሚኖርበትን 'ዛሬን' አሻግሮ ወይም አርቆ የማሰብ ችሎታ ነው ። በግለሰብ፣ በቤተስብ ፣ በማሕበረሰብ እና በሰከኑ መሪዎች ደረጃ በየትኛውም ታሪካዊ ዘመን (**chronological**

**time)** ይኑሩ - የየትኛውም አገር ዜጎዎች ወይም ሰዎች ስለሚኖሩበት ዘመን ፍላጎታቸውን በማሟላትና በማሰብ ብቻ አይኖሩም ። የሚኖሩት ከትላንቱና ከነገውን እነሱነትጋር በተዛመደና በተሣሰረ ሕይወት ውስጥ ነው ።

ሰዎች በየደረሱበት ዛሬ እየኖሩ በሕይወት ላልኖሩበት ስለትላንቱ እነሱነት እና በሕይወት ለማይደርሱበት ስለነገን እነሱነት እያሰቡና እየተጨነቁ ይኖራሉ ። ስለትላንቱ - አገራቸውን ፣ ታሪካቸው ን፣ ባህላቸውን ፣ ዕደገታቸውን ፣ ገድላቸውን ፣ እሴታቸውን ወዘተ.. ከደረሱበት የዛሬን እነሱነት እና ከማይደርሱበት - የነገን እነሱነት ጋር እያዛመዱ ፣ እያገናዘቡና እያሰቡ ይኖራሉ ።

በደረሱበት ዛሬ ላይ ሆነው ከመቶዎች ወይም ከሺዎች ዘመናት በፊት ጀምሮ የነበሩትን ቀደምቶቻቸውን ያወረሷቸውን ሁለአንተናዊ - የማንነት እሴቶቻቸውና ቅርሳቸውን ከነገው ትውልድ ማንነት ጋር የተሳሰረና የተቆራ ኘ **(intertwined or linked)** መሆኑን ስለሚያውቁ ተንከባክበው ፣ አዳብሮና አበልጽገው ለነገው ትውልድ ለማስረከብ ይጥራሉ ።ኖሮ ኖሮ ወደ ግብዓተ መሬት መግባት ብቻ ሳይሆን ጥሩ ነገር ለነገው ትውልድ አውርሶ ማለፍ የሰው ልጅ ማሰባዊ ባህሪና ልማዳዊ ግዴታ ።

ለምሳሌ- ቅድመ አያቶቻቸው ወይም አያቶቻቸውን በአደዋ ጦርነት ፤ አያቶቻቸው ወይም አባቶቻቸውን በማይጨው ወይም በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ጦርነት የተዋጉበትን - ውጅግራ ጠመንጃ ፣ ዝናር ፣ጋሻ ፣ ጦር ፣ጎራዴ ወዘተ..በእንክብካቤና በታላቅ ኩራት ይዘው የተቀመጡ በርካታ - የነኚያ ጀግኖዎች ቤተስዎች መኖራቸውን አልጠራጠርም ፤እኔም ከነዚያ ቤተሰብዎች አንዱ ነኝ ። ልጅ ከአባቱ፣አባት ከአያት፣አያት ከቅድመ አያት ወዘተ.. የተረከቡትን - ቁየ ፣ እርስት ፣ ጥሩ ሥራ ፣ መልካም ስም ፣ የአካባቢ ወይም የብሔራዊ ገድል ማስረጃ ቅርሶች ለልጆቻው አውርሰው /አስረክበው ያልፋሉ ።

በዛሬ ሕይወት ስለዛሬ ማንነት ማሰብ ፣ በዛሬ እየኖሩ ስለ ትላንቱ ማንነት ማሰብ ፣ በዛሬ እየኖሩ ስለነገን ማንነት ፣ ስለነገን ትውልድና አገር ማሰብ ወይም በአንድ የሕይወት ዘመን የሶስትዮሽ ሕይወት መኖር ከንውን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ- የነበረ ያለና የሚኖር ነው ።ያለ ፈውን ፣የዛሬውንና የመጪውን ጊዜያት/ዘመናት ሂደት - ክንውን በተፈጥሮ ህግ እንደመተሳ ሰር **(embeded)** እንደመሆን ማለት ነው ።

የዘመናችን ‘ገኀሮዎቻችን’ (ወያኔዎች) ግን ፤

ምስላቸው ሰው ቢመስልም፣

እንደ ሰው አንደበት ቢኖራቸውም፣

እንደ ሰው ቢበሉም ቢጠጡም፣

እንደ ሰው በሁለት እግር ቢራመዱም፣

ከአምባሻና ከሌሎች አገር በቀል ምግቦች ወደ አውሮፓ ሠራሽ ምግብ ቢሸጋገሩም፣

ውሃ ፣ጠላና አረቄ ከመጠጣት ወደ ቢራ ፣ውስኪ ፣ኮኛክና ሻፓኝ መጠጣት ቢሸጋገሩም፣

በጭቃ፣ በሳርና በቆርቆሮ ቤቶች ከመኖር ወደ ቪላ ቤቶች ቢሸጋገሩም፣

በወንዝና በምንጭ ውሃ ከመታጠብ - የፈረንሳይ ሻፓኝና ሽቶ በተቀላቀለበት ገንዳ ወሃ መታጠብ ቢችሉም፣

ቱታ፣ ቁምጣና ባህላዊ ልብሶች ከመልበስ - አውሮፓ ሥራሽ ሸሚዝ ፣ ክራባትና ሱፍ መልብስ ቢችሉም፣

ከአገር ሠራሽ ሰንደልዎችና ጫማዎች -አውሮፓ ሥራሽ ጫማዎች ቢጫሙም፣

በእግር ፣ በአህያና በበቅሎ ከመጓዝ - ድህረ ዘመናዊ አውርፓ ሠራሽ ምርጥ መኪናዎች መንዳት ቢችሉም፣

በኬሻ ፣በጠፍርና በንጨት አልጋ ከመተኛት - ድኅረ ዘመናዊ አውረፓ ሠራሽ አልጋ ፣ ፍራሽና አንሶላ ላይ ለመተኛት ቢበቁም፣

በቦርጭማ ፣በጠፍርና በአግዳሚ ወንበር ከመቀመጥ -ድኅረ ዘመናዊ አወሮፓ ሠራሽ ሶፋዎችና ወንበሮች ላይ ለመቀመጥ ቢበቁም፣

በባህላዊ ሰፌድና መሶብ አስቀምጦ በእጅ ከመብላት - አውሮፓ ሠራሽ ዘመናዊ ጠረጴዛዎች ፣ ሣህኖች ፣ ሹካዎች ፣ ማንኪያዎች ፣ ቢላዋዎች ወዘተ.. ተጠቅመው መብላት ቢችሉም፣

ከባህላዊ - ውሃ ፣ ጠላ ፣ጠጅ ፣ ቡና ወዘተ.. መጠጫዎች - ድኅረ ዘመናዊ አውሮፓ ሠራሽ - ቡና፣ውሃ ፣ ቢራ ፣ ውስኪ ፣ ሻፓኝ ወዘተ.. መጠጫ ሲኒዮችና ብርጭቀዎች ለመጠጣት ቢበቁም፣

ሰፊው የኢትዮጲያ ሕዝብ የሚበላበትና የሚጠጣበት መጠጥ ቤቶችና ሆቴሎች ንቀውና ተስፈንጥረው - በሻራተን ፣ በሂልተን ፣ በማሪዮት ፣ በሃራምቢ ፣ በግሎባል ወዘተ.. ሆቴሎች መብላት ፣ መጠጣት ፣ መደነስ ፣ ውለው ማደር ቢችሉም ፤ቢያዘወትሩም፣

ልጆቻቸው ወደ - አሜሪካ ፣ አውሮፓ ፣ አውስትራሊያ ፣ ካናዳ ፣ ኒዩዝላንድ ፣ እስካንዳኔቪያ ወዘተ.. አገሮች ልኮ ማስተማር ቢችሉም፣

በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር በተለያዩ ባእዳን አገራት ባንኮች ማስቀመጥ ቢችሉም ፣

እነዚህን ማድረግ መቻል ለወያኔዎች ትልቅ ሥልጣኔ ፣ ትልቅ እድገት ቢመስላቸውም ፣

ስው የመሆን መሥፈርት ጭራሽ አያሟሉ ም።

በዛሬ ላይ እየኖሩ ለዛሬ ሕይወት ምቾት ስለሚሰጥ ነገር ብቻ አድርጎ ወይም ተግብሮ መኖር - በማሰብ ሳይሆን በደመነፍስ /በዳበሳ መኖር ነው ።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሕልው ከሆኑባቸው (came into being) ታሪካዊ ወቅት ጀምሮ ፤ለብዙ ሺ ዓመታት የተገነባውና የተከማቸውን የአገራችንን (የዜጎችን የጋራ ሃብት) (the wealth of the nation) እና የዜጎችን የግል ሃብት - በወያኔ ጠቅልል ሥልጣን ወይም በመኖፖል በመያዙ ፤ ሕልው የሆኑበትን የተፈጥሮ አካባቢያቸውን እየበዘበዙና እየደመሰሱ ከሚኖሩ ደመ-ነፍስ ፍጥረታት በከፋ ሁኔታ እየበዘበዙና እየደመሰሱ (ቫንዳላይዝ) እያደረጉ ይገኛሉ ።

እኔ እጅግ በጣም የሚያሳዝነኝ ‘ለተራበ ጅብ ጥንብ ያዝለታል’ እንደሚባለ ው ፤ከላይ እንድገለጽኩት የሩቅና የቅርብ ቀደምቶቻችንና ወላጆቻችን -ያለጫማ በባዶ እግራቸውን እየሄዱ ፣ያማራቸውን (ሳይለብሱ ፣ ሳያጌጡ፣ ሳይበሉና ሳይጠጡ) ፤ ከእርስታቸው ኩርማኑን መሸጥ እንድ ውርደት ቆጥረውና ቤተሰባቸውን- አስርበውና አሳርዘው -ለልጅ ፣ለልጅ-ልጂ ምን ትቼ ወይም አውርሼ ልለፍ እያሉና እየተጨነቁ ያቆዩልንን ፤ከቤተሰብ ትውልድ ሰንሰለት ሲወርዱ ሲዋረዱ (ሲወራረሱ) የመጡትን የተከማቸ ጥሬ ሃብት (በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ) ፣ቋሚ የሃብት ምንጮች ማለት የገጠርና የከተማ መሬቶች ፣ማዕድ ኖች ፣ ዛፎች ፤ደኖች ፣ ወንዞች ወዘተ.. የወያኔ ቤተሰብና የጎሳ አባሎቻቸ ውን ብቸኛ - የመደላቀቂያ ሲሳይ መሆናቸውን ነው ።

ወያኔ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ልማዳዊ ሕይወት ከፉኛ አዛብቷል/ኢቃው ሶል ፤ድሮ እኔ ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ- አንድ የገበሬ ቤተሰብ በአማካይ ከ 20 -50 የቀንድ ከብቶች ያረባ ነበር ፤ወያኔ ለሥርወ-ስልጣን ከበቃ ጅምሮ የግጦሽ መሬቶች ከገበሬዎች ነጥቆ ለአባላቱ ፣ለትግራይ ተወላጆች እና ለውጭ ኢንቬስተሮች ስለተቸበቸበ ፤ ገበሬው ከአንድና ከሁለት የቀንድ ከብት በላይ ማርባት አልቻለም ፤አይችልምም ።

ቁንጮ ወያኔዎች ፣ቤተሰባቸው ፣አባሎቻቸውና ለወያኔ ያደሩ የጀርባ አጥንት/ከረከር የለሽዎች - በሃብት ምንያህል እንደደለቡና የሕይወታቸውን ቅንጦት ሲነገርና ሲሰማ ፤ ወያኔ የሃገራችንን ብሄራዊ ሃብትና ንብረት በራሱ በወያኔ አገዛዝ ዘመን ማለቅ አለበት ብሎ የወሰነ ይመስላል ። ከእናት ኢትዮጵያ መሃፀን የተገኙትን ሃብቶች መበዝበዝ ብቻ ሳይሆን እራሷ እናት ኢትዮጵያንም እየተቸበቸበች በምድር ገነት ይኖራሉ (ግብረ ወያኔ) ። ወያኔ ጥንታዊና ዘመናዊ -የትምህርት ፣የግብ ርና ፣የመከላኬያ ፣የምህንድስና የመገናኛ ወዘተ.. መሣሬያዎችን ሰብስቦና ነቃቅሎ ወደ መፈጠሬያው ትግራይ አጓጓዟል ፤የታሪክና የኪነጥበባት መጽሃፍት አቃጥሎዋል ፤ለም አፈር ፣ ምርጥ ለልማትና ለቤት መሥሬያ የሚውሉ ዛፎችን ወደ ቀዬው አስጭኗል ፤ በትጥቅ የሚታገሉትን ሃይሎች ይጠለሉበታል የሚላቸውን -ውብ ጫካዎችና ደኖችን መንጥሯል ፤ አቃጥሎዋል ። ወያኔ የደመሰሰው - ለብዙ ሺ ዓመታት ከትውልድ ወደ ትውልድ ‘ሁልእንትናዊ ኢትዮጵያዊነትን ተሸክመው የተጓዙትና መተኪያ የማይገኝላቸውን ተቋማት፣ የኪነት፣የባህል፣ የታሪክ ወዘተ. ቅርሳቅርሶችን ብቻ ሳይሆን -የአገራችንን የተፈጥሮ አካባቢ ደምስሷል ፤እየደመሰሰም ነው ( **vandalized and still vandalizing our natural environment)** ።

በሳይንሳዊ ሥልጣኔና በሳይንሳዊ ምርምር እየተመሩ ያደጉ አገሮች -የአካባቢ የተፈጥሮ ሃብትን/ቶችን የሚጎዱና የሚያመነምኑ እንስሣትና ፍጥረታት እያሳደዱ በመርዝና በጥይት በመግደል ቁጥራቸውን እንዲቀንስ ወይም ዝርያቸውን እንዲጠፋ ያደርጋ ሉ ። ወይም ሌሎች እነሱን የሚበሉ እንስሳት ወስደው ያሰፍራሉ /ያረባሉ ፤ ለምሳሌ ሚዳቅዎች ለእርሻና ለሣ ር እድገት ጠንቅ ስለሆኑ እነሱን ለማጥፋት በሥፍራው - ቀበሮዎች ወይም ጉጉሎች ወይም ጆፌ አሞራዎች ያሰፍራሉ/ያረባሉ ። ከዚህ ሳይንሳዊ አመለካከት አኳያ - ወያኔዎች በመርዝ ፣ በጥይትና እነሱን እያሸተቱና እያነፈነፉ የሚበሉ አውሬች ፈልጎ በእነሱ ላይ በመልቀቅ - መመንጠር ወይም መደምሰስ ይኖርባቸዋል ማለት ነው ።

የኢትዮጵያን -ሉዓላዊነትና ዳርድንበር መደፈር፣መልካምድር ተሸንሽኖ መሸጥ ፣የተፈጥሮ ሃብት መደምሰስ ፣ ጥንታዊ ቅርሶችና ተቋማት መፈራረ ስ ፤የኢትዮጵያውያንን -ክብር ፣ታሪክ ፣ ቋንቋ ፣ባህል ፣ ተፋቅረውና ተሳሳ ሮ መኖር ፣ ስለትላንቱ እና ስለነገው ማንነታችን ወይም እኛነት ወዘተርፈ መቆርቆር ለወያኔዎች ተረት ተረት ነው ፤ለምን ባፍጥማቸው አይደፋም ። እኛም ከእነሱ ይህንን አጠብቅም ፣ ከተግባራቸው ተምረናልና ፤እንዴት እንደ ደመነፍስ እንስሳት የሚበላውና የሚጠጣውን ብቻ አሳዶ ከሚኖር ሰው መሳይ ፍጥትረት ይህንን ይጠበቃል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ (በረሃብ ፣በእርዛትና በበሽታ ተጎሳቅሎ መሞት፣ የሚላስና የሚቀመስ ነገር ጠፍቶ ሲሰደዱ -በባህር መሥመጥና በአውሬች መበላት ፣በየባዕዳን አገሮች እስር ቤቶች መማቀቅ ፣ በተሰደዱበት በሰው አውሬ ተገለው ኩላሊታቸውና ጉበታቸውን እንደሸቀጥ መሸጥ ፣እስላም አይደላችሁም ተብለው በጅምላ መታረድ ፣የዘመኑ የአረቦች የጉልበትና የፍትሆተ ሥጋ ማርኬያ ባሬያ መሆን ፣ መሸከም ከማይችሉትን መከራ ለማምለጥ ከፎቅ ተፈጥፍጦ መሞት

ወዘተ.. የወያኔ ሥርዓት ውጤቶች መሆናቸውን- ወያኔዎች አይረዱትም ፤አይቀበሉትምም ።ሲያዝኑም አይታ ዩም ። እኛም ከእነሱ እውነትና ሰውኛ ኅሊና አንጠብቅም ፤ሰውኛ ባህሪ የላቸውምና።

ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ -ጀግኖቻችን ፣አንበሶቻችን፣ባለታሪኮቻችን ወዘተ..ናቸው እያለ የሚኮራባቸውን - እነሱ (ወያኔዎች) ግን የእነሱን ታሪካ ዊ ማንነት በማጥበብና በማሳነስ - ትግሬ ላልሆነ ሕዝብ ምኑም አይደሉም ፤ ታሪካቸው ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አይዛመድም የሚሉንን (አጼ የሓንስና ራስ አሉላ) እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ከባዕዳን ወራሪዎች ጋር የተፋለሙለትን 'ምጽዋን' ከሻቢያ ጎን ተሰልፈውና ተዋግተው -ለሻቢ ያ አሳልፈው ሰጡ ። የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢ ለመሆን ከበቁ ም በኋላ ኤርትራን በአዋጅ አስገነጠሉ ።

ለአጼ የሓኒስ የሚሰጥ የንግሥት ቪክቶሪያ መልእክት ይዞ ወደ አቢሲኒያ የተጓዘው {ጀራልድ ፖርታል} እ.አ.አ 1892 ዓ.ም 'ወደ አቢሲኒያ ልዑክነቴ' በተሰኘው መጻሓፉ -(ይዞት ስለሂደው መልዕክት፣ ስለአጼ የሖኒስና ስለ ራስ አሉላ) እንድ ሚከተለው ጻፈ።

መልዕክቱ -አጼ ዮሓኒስ በጣሊያኖች ተይዞ የነበረውን የጠረፍ ከተማ 'ጊሂንዳን' ወስደው -በምትኩ 'ሣሃቲ' በመባል ይጠራ የነበረውን የቀይ ባህር ጠረፍ መሬት ለጣሊያን እንዲሰ ጡ የሚጠይቅ ስለነበረ ፤ አጼ የሓኒስ እንኳንስ መሬት ሰጥተ ው ሊታረቁ - እንደዚያ መታሰቡን አስቆጥቷቸው "ጣሊያኖቹ ም ሆኑ ሌሎች ባእዳን 'ምጽዋን' ይዞ የመቆየት መብት የላቸው ም ። ምጽዋና ሁሉንም የደቡብ ምዕራቡ የቀይ ባህር ዳርቻዎ ች ለእኛነታቸው ታሪካዊ መብታችን ነው ። 'ከኢትዮጵያ መልካ ምድር መሬት ቆርሶ ወይም ሸንሽኖ የመስጠት **ዝንባሌም፣ መብትም፣ ሥልጣንም የለኝም**' !

ቱርኮች በጦር መሣርያ በልጠውን በመገኘታቸው ከ16 ኛውን መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንዲወጣ ቢያደረጉም -ያንን የተነጠቀውን መብታችን ለማስመለስ ከመጣር ኢትዮጵያ የተቆጠበበት ጊዜ ጭራሽ የለም።ምጽዋ በጣሊያኖች ሲወሰድ ቆሜ በዝምታ እንድመለከት ተጠየቅኩ ! ግብጾዎች ሲለቁ ምጽዋ ወደ ጥንትና ባለመብት ወደ ሆነው ሕዝቡ ይመለሳል!" ማለታቸውን {ጀራልድ| ጻፍ።

የራስ አሉላን አነጋገር ከአጼ የሓኒስን አነጋገር የከረረና ድፍረት የተሞላበት እንደነበረ ሲያስጨብጥ ፤ "ጣሊያኖች በደጓሌ ድባቅ መታኋቸው ! መልሼ እመታቸዋለሁ !እኔ የማውቀው የኢትዮጵያ የተፈጥሮ በር ቀይባህር መሆኑን ነው።ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ መሬት ማግኘት የሚችሉት 'እኔ የሮም ገዢ' ከሆንክ ብቻ ነው !" ብለዋል በማለት{ጀራልድ ፖርታል} መሰክሯል ።

ምንጭ ፤ (ጀራልድ ፖርታል፣ዳንኤል ክንዴ- የኤርትራ ግጭት አምስት አቅጣጫዎች ወይም አድማሶች፣1941-2004) በሚል እ.አ.አ በ(2005) ዓ.ም ከተጻፈ የእንግሊዘኛ መጽሃፍ

ከላይ በአጼ የሖኒሳና በራስ አሉላ የተገለጹትን- የፍጹም ኢትዮ ጵያዊነት (ጽንሰ ሃሳብ ፣ጀግንነት ፣የአገር ፍቅር መተከ ል ወዘተ..ናሙና) መልዕክቶች ለዛሬዎቹ ወያኔዎች ትርጉም ይሰጥ ይሆን? የአምሮ ሕዋሳቸውን ይነካ/ይዳሥስ ይሆን? አንብበውና ሰምተው ይርዱት ይሆን ?አይመስለኝም ! ምክንያ ያቱም አጼ የሖኒስና ራስ አሉላ- የሀገራችንን ዳርድንበር ላለማ ስደፈር የከፈሉትን መሰዋዕትነት እና የተውልንን -ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የፍጹም ኢትዮጵያዊነት ቋሚ የጀግንነትና የሀገር መውደድ አስተምሮት ታሪክ -የዘመናችን ወያኔዎች **አንብበውም ሆነ ሰምተው የመረዳት ብስለት ቢኖ ራቸው ኖሮ** ቢያንስ የኢትዮጵያን መልክዓምድር ልዑላዊነት ወይም ዳርድንበር ያስከብሩ ነበር ።

በይዘታቸውና በቅርጻቸው የተለያዩ ቢሆኑም - ስለወያኔዎች ማንነት ፣ ምንነት ፣ ባህሪ ፣ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ፣ወራሪነት ወዘተ..ለሃያ ስድስት ዓመታት በተለያዩ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ተጽፏል ።ለዚህ ጽሁፍ በሰጠሁት አርእስት ከሁለት

ዓመታት በፊት መጠኑ ከዚህ ያጠረ ተመሳሳይ ጽሁፍ ቢያንስ በአራት በኢትዮ-ዲያስፖራ ኅትመት ሚዲዎች ታትሞ ተነበዋል።

ይህ ጽሁፍ ስለወያኔ/ዎች ከተጻፉት ሌሎች ጽሑፎች ሁሉ የሚለየው 'ወያኔነትን' በሚመጥን (**compatiable**) በሆነ አርእስት መሰየሙ - ለተመሰለበት አርእስት በሚመጥንና በሚ ቀራረብ -ማስረጃ ተዛምዶና ተደግፎ መጻፉ ወይም መንጸባረ ቁ ነው ።የወያኔ/ዎች ደመነፍሳዊ ባህሪያትና ተግባራት በጢቂ ቱም ቢሆን ከላይ ስለገለጽኩት - ያንኑ አሳጥሬና ስብስብ አድርጌ በመነጠብ ይህንን ጽሁፉ እቋጫለሁ ። ይኸውም ወያኔ/ህወሃት፤

-ኤርትራን ፣ምጽዋን ፣አሰብና የሰሜን ምዕራብ መልክዓምድራ ራችንን አሳልፎ በመስጠት አገራዊ/ብሄራዊ ልዑላዊነታችን አስ ደፍሯል/አስነጥቋል

-ጥንታዊና ዘመናዊ -የመከላኪያ ማለት (የምድር ጦር ፣ የአየር ኃይል ፣ የባህር ኃይል) ፣የመገናኛ ፣የግብርና ፣የትምህርት ወዘተ.. ተቋማት አፍርሷል

- ጥንትዊና ዘመናዊ ኢትዮጵያዊነትን የተሸከሙ -የታሪክ መጽ ሃፍት አቃጥሎዋል ፤ የባህላዊና የኪነጥበባት ቅርሳቅርስ እሴቶቻንን አውድሟል

- ሕዝባዊ ፣ባህላዊ ፣ማኅበራዊ ፣ሥነልቦናዊ ፣ሃይማኖታዊ ወዘ ተርፈ ትሥሥራችን ላይ መርዝ ረጭቷል ፤ እንዳንተማመንና አብረን እንዳንኖር አድርጓል

- በፀረ ብሄራዊ ቋንቋችን ላይ ዘምቷል ፤ ለማዳከም ጥርሯል

-ባንድራችንና ታሪካችን -አንቋሿል ፤ ክዷ

-ለአገሩ ፣ለባህሉ፣ ለታሪኩ፣ለሕዝቡ፣ ለቋንቋ ፣ለትላንቱና ለነገው ማንነቱ የማይቆረቆርና የማያስብ፣ራሱን የሚወድና ለዛሬ ሕይወቱ ብቻ የሚያስብ ወጣት ለመቅረጽና ለመኮትኮት ጥሯል ፤እየጣረም ነው ።

-ለብዙ ሺ ዓመታት የተከማቸ የዜጎችን የጋራ ብስል ሃብት-ማለት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ( **the wealth of the com mon- capital in the nation's banks**) ወደ ኤፈርትና ረስ ት ኩባኒያዎች ኮረጆ ገልብጧል ፤ቁጥጥር ሥር አውሎዋል

- በግብርና ፣በፋብሪካ፣ በከብት እርባታ፣ በንግድ፣ በሃይል ማመንጫ፣ በኢንዱስትሪ ወዘተ.. ዘርፎች የኢትዮጵያውያንን ጭንቅላትና ጉልበት በመበዝበዝ የሚገኘውን -አቢይ ሃብት ወይም ገንዘብ (**labour capital**) እንድግል ሃብታቸው ተጠቅ መውበታል

-የሃገራችን የሃብትምንጮች ማለት መሬቶች ፣ማዕድኖች ፣ ደኖች፣ ዛፎች ፣ ወንዞች ወዘተ ሽጧል ፤አውድሟል

-ለም አፈር ፣ለቤት መሥሬያና ለልማት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ትን ዛፎች- ከሁሉንም የኢትዮጵያ ምድር ወስዶ ወደ ትግራይ አጓጓዘ ፤ ጫነ

-ጠመንጃ ያነሱ ተቃዋሚዮች መጠሌያ ይሆናሉ ያላቸውን -የአገራችንን የተፈጥሮ ፀጋና ውበት የነበሩ -ጫካዎችና ደኖች አቃጥሎ አውድሞዋል

- ስለማይደርሱበት -መሸጥና ማውደም ያልቻሉት የኢትዮጵያ ሰማይ ብቻ ነው

ሁሉም እብድ ናቸው እንዳንል ፤ዕብድ ራሱንና በአጠገቡ ያለ ሰው ይጎዳ እንደሆን እንጂ የሚኖርበትን ቤትና አካባቢዩን አያፈርስም/ አያወድምም ፤ ወራሪዮች እንዳንላቸው -ወራሪዎ ች/ቅኝ ገዢዮች -በቅኝ የገዙትን ሕዝብ ይጨቁናሉ እንጂ በቅ ኝ የገዙትን አገር አያስገነጥሉም ፣ የዚያን አገር የባህር በር አያስወስዱም ፣ የዚያን አገር የተፈጥሮ ሃብት አያወድሙም ደቡብ አፍሪካ በምሳሌት መመልከት ይቻላል ። ትግራይን ለመጥቀም ግን ሰው ይሆናሉ እንዳንል -ኢትዮጵያና ኢትዮጵ ያዊነት ከሌለ ትግሬና ትግሬያዊነት ሊኖሩ እንደማይችሉ ማሰ ብ አልቻሉም ። ስለሆነም ወያኔዎች ለሚኖሩበትን ዛሬ ምቾታ

ቸውን ብቻ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እያፈረሱና እየደመሰሱ ስለሚኖሩ በደመነፍስ ወይም በዳበሳ ከሚኖሩ እንስሳት ወይ ም ፍጥረቶች አይሻሉም እላለሁ ።

ወያኔዎችም ኢትዮጵያን - በመበዝበዝ ፣ሸንሽኖ በመሸጥና በመደምሰስ ‘ለዛሬ ቅንጦታቸውን ብቻ ስለሚኖሩ

በደመነፍስ ወይም በዳበሳ ከሚኖሩት ፍጡሮች አይሻሉም ።

በደመነፍስ የሚኖሩ ፍጡሮች (ግኝትዎች)ማሰብ ስለማይችሉ - ሕልው የሆኑበትን ወይም የተፈጠሩበትን አካባቢ በመበዝበዝና በመደምሰስ እንደሚኖሩ ሁሉ።